## *የኦሮሞ ህዝብ ትግል ትላንት ዛሬም ሆነ ነገ በጨቁዋኝ ስርኣቶች እንጂ በማናቸውም ህዝቦች ላይ ኣያነጣጥርም*

የኦሮሞ ህዝብ በጭቆና ቀንበር ስር ከወደቀበት ጊዜ ኣንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ እየታገለ ያለው የጭቆናውን ስርኣት የዘረጉበትን ስርኣቶች እንጂ ስርኣቶቹ የተወለዱበትን ህዝብ ወይም ህዝቦች ኣይደለም። ኦሮምያን ወርሮ የኦሮሞን ህዝብ ለባርነት የዳረገው የነፍጠኛው ስርኣት የተወለደው ከኣማራው ብሄር ኣብራክ መሆኑ የሚታወቅ ነው። ይሁንና ኦሮሞ ለባርነት የዳረጉኝ ስርኣቶች የተወለዱት ከኣብራክህ ነው ብሎ ኣማራውን እንደ ብሄር ወንጅሎት ኣያውቅም። ይህን ስንል ታዲያ የብሄሩ ኣባላት የሆኑና ጨቁዋኙ ስርኣት በኦሮሞና በሌሎቹ ብሄር ብሄረሰቦች ላይ የዘረጋውን የጭቆና ስርኣት ገቢራዊ በማድረጉ እንቅስቃሴ ውስጥ የበኩላቸውን ተሳትፎ ያደረጉ ወገኖች ከስርኣቱ ተለይተው ሊታዩ ኣይችሉም። ከዚህ በተረፈ ግን የኣማራ ህዝብ ኣንደ ኣንድ ብሄር ይታወቃል እንጂ ከኣብራኩ ተፈጥረው ሌሎች ህዝቦችን ለጭቆና ከዳረጉት ስርኣቶች ጋር ኣንድ ላይ ኣይወገዝም።

ዛሬ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣን ጨብጦ የሚገኘውን ስርኣትም ኣስመልክቶ ያለው እውነታ ከዚህ የተለየ ኣይሆንም። ኦሮምያን በጭቆና ሰንሰለት ጠፍሮ እየዘረፈና ህዝቡንም በጠመንጃ ሃይል ኣንበርክኮ እየገዛ የሚገኘው የህወሃት ስርኣት ከትግራይ ህዝብ ኣብራክ የወጣ በመሆኑ ብቻ የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ የኦሮሞው ጠላት ኣይደለም። የህወሃትን የጭቆና ፖሊሲ በኦሮምያ ተግባራዊ በማድረጉ እንቅስቃሴ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተሳትፎ ያደረጉ ወገኖች ግን ከዚህ ወንጀለኛ ቡድን ተለይተው የሚታዩ ኣይሆኑም። በተረፈ ግን የትግራይ ህዝብ የጨቁዋኙ ወያኔ መፍለቂያ በመሆኑ ብቻ በጭፍኑ ተወንጅሎ በጠላትነት ኣይፈረጅም።

ከላይ የተጠቀሱትን እውነታዎች ያነሳነው ያለምክንያት ኣይደለም። ባሁኑ ጊዜ የኦሮሞ ህዝብ ፍትሃዊ ትግል በመፋፋሙ ቁጭትና ጭንቀት ኣድሮባቸው ተስፋ የቆረጡ የሚመስሉ ኣንዳንድ ወገኖች የኦሮሞን ትግል ኣላማ ኣቅጣጫ ኣዛብተው የማይገባውን ስም እየሰጡት ኣስነዋሪ ፕሮፓጋንዳ ሲነዙ ይሰማሉ። ለኣማራው ህዝብ ደህንነት የተቆረቆሩ ኣስመስለው የኦሮሞን ህዝብ ትግል በመወንጀል ተግባር ላይ የተሰማሩ እነዚህ ወገኖች ኣውቀውም ይሁን ሳይታወቃቸው በንብ ቀፎ ላይ ድንጋይ የመወርወር ያህል ስህተት እየፈፀሙ ናቸው። እነዚህ ወገኖች የኦሮሞ ህዝብ የሚታገልለትን ፍትሃዊ ኣላማ የሚቃረኑ በሃሰት የተቀነባበሩ ቪድዮዎችና ፅሁፎችን ኣዘጋጅተው በማሰራጨት ህዝቦችን ኣሳስተው ጦር ለማማዘዝ ደፋ ቀና ሲሉ ይታያሉ።

ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል በቅርቡ ራሱን *"ምረሽ ኢንቬስቲጌቲቭ ዩኒት"* እያለ በሚጠራ ኣካል በኣስነዋሪ መልኩ በሃሰት ተቀነባብሮ በ *youtube* ላይ የተለቀቀ ኣንድ ቪድዮ መውሰድ ይቻላል። ቪድዮው በኦነግ የሚመራውን የኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል በጭራቅነት ለመፈረጅ የተቻለለትን ጥረት ሁሉ ኣድርጉዋል። ሙሉ በሙሉ በሃሰት የተቀነባበረው ይህ ቪድዮ የኦሮሞ ህዝብ በገዛ ሃገሩ ላይ

ብሄራዊ መብቱን ለማስመለስ የሚያደረገውን ያልተቁዋረጠ ትግል “በአማራ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ የዘር ፍጂት (genocide)” በማለት በሚያሳዝን መልኩ ተርጉሞታል። ቪድዮው ይህንን ከሃቅ የራቀ ትርጉዋሜውን ለማጠናከር የተጠቀማቸው ስልቶች ደግሞ በይበልጥ አስነዋሪ ናቸው። ዘግናኞቹን የጀርመን፣ የቦስኒያ፣ የካምቦዲያ፣ የሩዋንዳና የመሳሰሉት የአለማችን የጅምላ ጭፍጨፋዎችን በተመለከተ እንደ ሲ ኤን ኤን ያሉ ቴሌቪዢኖች ቀደም ሲል አቀርበዋቸው የነበሩትን ዝግጅቶች በኦሮሞ ህዝብ ትግል ላይ ያነጣጠሩ ወግዞቶች አስመስሎ ለማወናበድ ሞክሯል ቪድዮው። የኦሮሞን ህዝብ ትግል አስፈላጊነት በተመለከተ ብሄርተኞች በተለያዩ መድረኮች ላይ ተገኝተው ያሰሟቸውን ንግግሮች ለጅምላ ጭፍጨፋ ህዝብን ያነሳሱ አስመስሎ በአሳፋሪ መልኩ ጠምዝዞ አቅርቦታል። በቪድዮው መልእክት መሰረት ኦሮሞ በሃይማኖትና በወንዝ አንከፋፈልም ብሎ ስለ አንድነቱ መቀርቀር በአማራው ብሄር ላይ ያነጣጠረ የጅምላ ጭፍጨፋ ጥሪ ተደርጎ ተወስዷል። እንደ ሃሰን አሊ ያሉ የኦፒዲኦ ካድሬዎች ንግግር ሳይቀር በኦሮሞነታቸው ብቻ ተለቅሞ በዚህ ቪድዮ ውስጥ ተካትቷል። በአንፃሩ የወያኔ መሪዎችና የመንግስቱ ሃይለማሪያም ንግግሮች ደግሞ በአጋርነት ተጠቅሰው በኦሮሞ ህዝብ ትግል ቅልበሳ ፕሮፓጋንዳው ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል።

የቪድዮው አዘጋጆች የራሳቸውን ድምፅ በመጠቀም በኦሮሞ ተወላጅነት ራሳቸውን መስለው ፀረ አማራ የሆኑ መርዘኛ ንግግሮች ቀርፀው ከኦሮሞ ብሄርተኞች ምስል ጋር በማቀናጀት ህዝብን ለማሳሳት ጥረዋል። ያን በሌላ ሰዎች የተነገረውን መርዘኛ መልእክት ብሄርተኞቹ የተናገሩት ለማስመሰል መሆኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ቪድዮው ወያኔ ሆን ብሎ ኦነግን በሽብርተኛነት ለመወንጀል ሲል ራሱ በሃሰት ያቀነባበረውን የጭካኔ ተግባር ሰለባዎችን ምስል በመጠቀም የስርኣቱ ልሳን እስኪመስል ድረስ ህዝብን ለማወናበድ ጥረት አድርጉኣል። ባጭሩ የዚህ ቪድዮ አላማ የኦሮሞ ህዝብ የተረገጠውን መብቱን ለማስመለስ ለረጅም ዘመናት የተያያዘውን ያልተቁዋረጠ ፍትሃዊ ትግሉን ከጀርመን ናዚዎች፣ ከካምቦዲያ ከሜር ሩዦችና ከሩዋንዳ ሁቱዎች ጋር ለማመሳሰል መድከም ነው። ከዚህ ሃሰተኛ ቪድዮ በግልፅ የሚታይ ነገር ቢኖር የቪድዮው አቀነባባሪ አካል ለኦሮሞ ህዝብ ያለው ጥልቅ ጥላቻ ነው። እንደዚህ ያሉት አካላት በጥላቻ ጥሪ ላይ ያተኮሩ ተመሳሳይ መልእክቶችን በፅሁፍ መልክም አዘጋጅተው በኢንተርኔት ድረ ገፆች ላይ በማሰራጨት የሚታወቁ ናቸው።

በ 2005ቱ ምርጫ ወቅት ተሳታፊ የነበረው የቅንጅት ፓርቲ ወደ ማሸነፉ በተቃረበበት ወቅት የወያኔ ካድሬዎች ፓርቲውን ኢንተር-ሃሙዌይ እያሉ በመጥራት ሲወነጅሉት እንደነበረ አይዘነጋም። በወቅቱ የአማራ ፓርቲዎች የትግራይን ህዝብ ከምድረ ገፅ ለማጥፋት ከሩዋንዳው ሁቱ መሪዎች ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጭፍጨፋ ጥሪ እንዳሰሙ ተደርጎ የትግራይን ህዝብ በሰፊው አነቃንቆ ከህወሃት ጎን ለማሰለፍ የተሰራው ስራ ቀላል አልነበረም። በተመሳሳይ መልኩ የኦሮሞ ህዝብ ትግልም ወጥሮ በሚይዛቸው አጋጣሚዎች ሁሉ እኛ ስልጣን ከለቀቅን ኦሮሞው ከምድረ ገፅ ያጠፋሃል እያሉ የትግራይን ህዝብ በማስፈራራትና በማሳሳት ከስርኣታቸው ጎን ለማሰለፍ ከንቱ ፕሮፓጋንዳ ማራገብ የወያኔዎቹ ባህሪይ ነው። ከላይ የተጠቀሰው በአማራ ህዝብ ስም የአዞ እምባ እያነባ የኦሮሞን ህዝብ ፍትሃዊ ትግል ለመወንጀል በከንቱ የሚዳክረው ቡድንም

ትላንት ወያኔዎች የተጠቀሙትን የስልጣን ላይ መቆያ ፈሊጥ እንደወረደ በመኮረጅ ሊጠቀምበት ዳዴ ሲል ትዝብት ላይ ወድቋዋል።

ሁለቱን ቡድኖች ማለትም ከኣማራና ከትግራይ ብሄር ኣብራክ የወጡትን የፖለቲካ ተዋናዮች ከሚያመሳስሉ ነጥቦች መካከል ኣንዱ ቀደም ሲል የተጠቀሰው ምሳሌ ነው። የህዝቦች ትግል ኣንቆ በያዛቸው ቁጥር ከውድቀት ራሳቸውን ለማዳን ሲሉ ከኣብራኩ የወጡትን ህዝብ ኣሳስተው ከጎናቸው ለማሰለፍ የቁራ ጭሂታቸውን ያስተጋባሉ። ህዝቦች ለመብታቸው መከበር የሚያደርጉትን ፍትሃዊ ትግል የጅምላ ጭፍጨፋ እንቅስቃሴ እያሉ መጥራት ኣያሳፍራቸውም። እገሌ የተባለው ብሄር ከምድረ ገፅ ሊያጠፋህ እየተዘጋጀ ነው በማለት ቆመንለታል የሚሉትን ክቡር ህዝብ ኣወናብደው የፖለቲካ ቁማር መጫወቻ ሊያደርጉት ይፈልጋሉ።

በኦነግ የሚመራው የኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ከቶ ሊቀለበስ ከማይችልበት ደረጃ መድረሱ ለጠላቶቻችን ምን ያህል የእግር እሳት እንደሆነባቸው በኣግራሞት ጭምር እየታዘብን ነው። የኦሮሞ ህዝብ የብሄርተኝነት ስሜት ጎልብቶ ለማንኛውም የባእዳን ማደናገሪያ ስልቶች ከማይበገርበት ደረጃ ላይ መድረሱ በነዚህ ወገኖች ላይ ይህ ነው የማይባል ጭንቀት ለቁዋል። በመሆኑም በቀቢፀ ተስፋነት ተነሳስተው ለኦሮሞ ህዝብ ፍትሃዊ ትግል የማይገባውን ኣስነዋሪ ስም ሊለጥፉበት ቢጥሩ ኣያስገርምም። ሲያሻቸው “የጅምላ ጭፍጨፋ” ኣልያም “ሽብርተኝነት” ሲሉት እየሰማናቸው ነው። እነዚህ ሁሉ ውሸቶች ኣንድ ላይ ተደምረው ትግሉን ከጎዳናው የማስወጣት ሃይል የላቸውም። የኦሮሞ ህዝብ ትግል ማንኛውም ጤናማ ህሊና ያለው ወገን እንደሚረዳው ኦሮሞው በገዛ ሃገሩ ላይ የተነፈገውን ብሄራዊ መብት ከማስመለስ በቀር ሌላ ሴይጣናዊ ኣላማ የለውም። ጭቆናን ኣላማቸው ያደረጉ ቡድኖችን ወይም ስርኣቶችን ለመታገልና ለመፋረድ እንጂ ኣልፎ ሄዶ እነርሱ የወጡበትን ህዝብ ለመጉዳት ኣልያም ለመበቀል ያለመ ትግል ኣይደለም።

ከትላንት ጀምሮ እስከ ዛሬ በዘለቀው የኦሮሞ ህዝብ የጭቆና ታሪክ ውስጥ ጨቁዋኝ ስርኣቶች በኦሮሞ ህዝብ ላይ የፈጽሙት ግፍና ወንጀል ተቆጥሮ የሚያ ልቅ ኣይደለም። የኦሮሞን እናት ጡት ቆርጠዋል። የኦሮሞን ወንዶች እንደ ከብ ት ኣኮላሽተዋል። እጁን ቆርጠው ኣንገቱ ላይ ኣንጠልጥለዋል። መንደሮችን ኣንድ ላይ በማጋየት ነዋሪዎችን በጅምላ ፈጅተዋል። በገንዘብ ተተምኖ የማያልቅ የኦሮምያ ሃብት ንብረት ዘርፈው ሲከብሩበት ባለሃብቱ የሆነው ኦሮሞው ግን በድህነት እንዲማቅቅ ፈርደውበታል። ነዋሪው ህዝብ በገዛ ሃገሩ ላይ ያለውን የፖለቲካ መብት እንዳሻቸው በማፈን ገዝተውታል። በጥቅሉ ወራሪዎቹ ስርኣቶች ኣያሌ የጦር ወንጀሎች (War crimes)ና የሰብኣዊ መብት ረገጣዎችን (Crimes against humanity) ከመፈፀም ኣልፎ መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ ዘረፋዎችን ኣካሄደዋል፣ ዛሬም በዚሁ እንደቀጠሉ ናቸው።

ኦነግ የሚታገለው በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተፈፀመውና ዛሬም በመፈፀም ላይ የሚገኘው ይህ መጠነ ሰፊ ግፍና በደል እንዲያበቃ ነው። ኦሮሞው የታፈኑ መብቶቹን በሙሉ ኣስመልሶ እንደማናቸውም የኣለማችን ህዝቦቹ ኣንገቱን ቀና ኣድርጎ እንዲኖር ለማስቻል ነው። ከዚህ ባሻገር ብቀላ የኦነግ የትግል ኣላማ

ኣይደለም። ኦነግ ደጋግሞ ሲገልጽ እንደኖረው ኣይንህን ያጠፋ ጠላት ኣይኑን ኣጥፋ የሚል የሃሙራቢ ህግ የሚከተል በብቀላ የሚያምን ድርጅት ኣይደለም። የኦሮሞ ህዝብም በመሪ ድርጅቱ ኦነግ ስር ተደራጅቶ እየታገለ የሚገኘው በገዛ ሃገሩ ላይ መብቶቹን በሙሉ ነጥቀው ያዋረዱትን ቡድኖች ከላዩ ላይ ለማንሳት እንጂ ኣልፎ ሄዶ ቡድኖቹ የፈለቁበትን ህዝብ ወርሮ ለመያዝ ኣልያም የትላንቱን በደል ለመበቀል ኣይደለም። ኦሮሞ በሃገሩ ኦሮምያ ምድር ላይ የሚያደርገው የመብት ትግል ደግሞ ፍትሃዊ ትግል መሆኑን መካድ ኣይቻልም። ለዚህ ፍትሃዊ ትግል የሚሰጥ ጭራቃዊ ስም በማንኛውም መስፈርት ተቀባይነት ኣይኖረውም። የዚህን ትግል ፍትሃዊነት በሚገባ እያወቁ ሌላውን ወገን ለማወናበድ ኣንዳንዴ “ሽብርተኛነት” ሲያሻቸውም “የጅምላ ጭፍጨፋ” የሚሉት ቡድኖች መልሰው ራሳቸውን እያሞኙ ናቸው። ትላንት በኣያቶቻቸው የተፈፀመውን ዘግናኝ ወንጀል ለመሸፋፈን ሲሉ የዚህን ትግል ፍትሃዊነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ለማስገባት የሚያደርጉት ጥረት ከቶ ሊሳካላቸው የሚችል ኣይሆንም። በክፋት በተሞላ በዚህ ኣይነቱ ኣካሄድ የትላንቱን የኦሮሞ ህዝብ ቁስል እንጨት እየሰደዱበት ማድማት የህዝቡን ቁጣ ለማስገንፈል ካልሆነ በቀር ትግሉን ለኣንዲት ስንዝር ወደሁዋላ መመለስ ኣይችልም።

እንደዚህ ያሉት ወገኖች በመጀመሪያ ደረጃ የወጡበትን ህዝብ በብሄሩ ስም እየጠሩት ቆመንለታል ማለታቸው መብታቸው ነው። ቀደም ሲል ኣማራ የሚባል ብሄር የለም እያሉ መላውን ኢትዮጵያ ርስታቸው ለማድረግ ኣስበው የህዝቦችን ማንነት በመካድ በ “ኢትዮጵያዊነት” ብቻ ራሳቸውን ሲገልፁ እንደነበረ ይታወቃል። ዛሬ የብሄራቸውን ስም ጠቅሰው እንደቆሙለት መናገራቸው ሃጢያት ኣይደለም። ይሁን እንጂ የኦሮሞ ህዝብ ትግል እነርሱ የወጡበትን ብሄር ኢላማው ያደረገ ኣስመስለው እውነትን እያወቁ ኣዛብተው ለማቅረብ መሞከራቸው ያስጠይቃቸዋል። የኦሮሞ ህዝብ የተነፈገውን መብቱን ለማስመለስ የሚያደርገውን ፍትሃዊ ትግል ጥላሸት ቀብተው “የጅምላ ጭፍጨፋ ዘመቻ” ካሉት ራሳቸው በኦሮሞ ህዝብ ላይ የጅምላ ጭፍጨፋ እያወጁ መሆኑ ይግባቸው። “ሽብርተኛነት” ካሉትም ትርጉሙ ኦሮሞን በጭራቅነት ፈርጀው በሌላው ሁሉ ወገን በጥርጣሬ ኣይን እንዲታይና ተነጥሎ በቀላሉ እንዲጠቃላቸው የማድረግ ስልታቸው መሆኑ ነው። በነዚህ ሁለቱ የስም ማጥፋት ልፈፋዎች ሳቢያ ነገ ሊከሰት ለሚችለው ኣደጋ ታድያ ውሎ ያድራል እንጂ ከተጠያቂነት ኣያመልጡም።

በዚህ ኣጋጣሚ ለኣማራው ወንድም ህዝብ የምናስተላልፈው መልእክት ግልፅና ኣጭር ነው። የኦሮሞ ህዝብ ትግል ከኣብራክህ ወጥተው በህዝባችን ላይ ዘግናኝ ወንጀል በፈፀሙና ዛሬም ያን ወንጀላቸውን ለማደስ ደፋ ቀና በሚሉት ቡድኖች ምክንያት እንደ ብሄር ባንተ ላይ ኣያነጣጥርም። ከኣብራክህ ወጥተው በወንጀል ላይ ወንጀል ለመድገም የሚሯሯጡ ወገኖችን ግን መክሮ ወደቀናው ጎዳና የመመለስ ሃላፊነት ያንተ መሆኑን ማስታወስ እንወዳለን።

ለትግራዩ ወንድም ህዝብም ያለን መልእክት ከዚህ የተለየ ኣይደለም። ወያኔው በነፃ ህዝቦች ላይ እየፈፀመ ላለው መጠነ ሰፊ ወንጀል የትግራይ ህዝብ እንደ ህዝብ ልትጠየቅበት ኣትችልም። ይሁንና ታድያ ከኣብራክህ ወጥተው ይህንን ባንተ ላይ እንዲፈፀም የማትፈቅደውን ወንጀል በሌላው ላይ የሚፈፅሙትን ልጆችህን በቃችሁ ማለት ያንተ ፋንታ መሆኑን ሳናስታውስህ ማለፍ ኣንችልም።

ባጠቃላይ የኦሮሞ ህዝብ ትግል ትላንት፣ ዛሬም ሆነ ነገ በጨቁዋኝ ስርኣቶች እንጂ በማናቸውም ህዝቦች ላይ የማያነጣጥር መሆኑን ወዳጅም ሆነ ጠላት እንዲገነዘብ እንሻለን።

ድል ለኦሮሞ ህዝብ!

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ